# የግብረገብ ትምህርት
## የተማሪ መጽሐፍ
## 2ኛ ክፍል


### ተርጓሚዎች

አስመራ ቤጊ

በርናባስ ደበሎ

ቶለረቢ መኮንን

አለሙ አብዲሳ

### አርታዒዎች

ትጃኒ ምትኩ

የኔነሽ ሳሙኤል

### ገምጋሚ

ደረጀ መኮንን ዴሬሳ

### ግራፊክስ

ታደሰ ድንቁ

### ገላጭ ስዕል

ብዙአየሁ ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2015/2023

ይህ መጽሐፍ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በ2015/2023 ተስማምቶ ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው። የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው። ይህን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፍቃድ በየትኛውም መልኩ ማሳተምም ሆነ ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

## ምስጋና

ይህ መጽሀፍ በትምህርት ሚኒስቴር አመራርና መነሻነት በሀዋሳ ፣ጅማ፣ አዲስ አበባና ባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው፡፡ በመቀጠል በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ቅንጅት ተተርጉሞና ተስማምቶ ተዘጋጀ፡፡

ስለዚህ በዚህ ስራ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው የትምህርት ሚኒስቴር፣ የዩኒቨርስቲ አዘጋጆችና በክልላችን ላሉ የትምህርት ባለሙያ ተርጓሚዎችና አስማሚዎች በሙሉ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ላቅ ያለ ምስጋና አለው፡፡

# መውጫ


ይዘት ገጽ

**ምዕራፍ 1፡- የራስን ክብርና ደህንነት መጠበቅ......1**

ትምህርት 1. ክብር........................................................1

ትምህርት 2. የአክብሮት አስፈላጊነት..................................7

ትምህርት 3. አክብሮትን ማሳያና ማሳደግያ መንገዶች.......9

ትምህርት 4. የራስን ደህንነት መጠበቅ............................14

ትምህርት 5. የህጻናት ደህንነት መጠበቂያ ዘዴዎች...........17

**ምዕራፍ 2:- እውነተኛነት እና ታማኝነት............23**

ትምህርት 1. እውነተኛነት እና ታማኝነት ምንነት.................23

ትምህርት 2. የእውነተኛነት እና የታማኝነት ማሳያዎች........24

ትምህርት 3. ቃልኪዳንን ማክበር.......................................30

ትምህርት 4. መስረቅ እና ማጭበርበርን መጥላት..................35

**ምዕራፍ 3:- ፍትህ .........................................38**

ትምህርት 1. የፍትህ ምንነት............................................38

ትምህርት 2. ፍትሃዊነት..................................................46

**ምዕራፍ 4:- መልካም ማህበራዊ ግንኙነት............49**

ትምህርት 1. ጓደኝነት....................................................49

ትምህርት 2. መረዳዳት...................................................54

ትምህርት 3. ጓደኝነትን የሚጎዱ ነገሮች.............................60

ምዕራፍ 5 ፡- ለጋራ ንብረት መጠንቀቅ................64
ትምህርት 1.የጋራ ንብረት..............................................64
ትምህርት 2.ውሃ.......................................................66
ትምህርት 3. ትምህርት ቤት........................................68
ትምህርት 4. መንገድ..................................................70
ምዕራፍ 6 ፡- ባህላዊ ቅርሶች...........................75
ትምህርት 1. የባህላዊ ቅርሶች ምንነት................................75
ትምህርት 2. የባህላዊ ቅርስ ዓይነቶች..................................79
ትምህርት 3. የባህላዊ ቅርስ ጥቅም.....................................82
ትምህርት 4. ባህላዊ ቅርሶችን መንከባከብ...........................85

# ምዕራፍ 1

# የራስን ክብርና ደህንነት መጠበቅ

## የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

- የክብርን ምንነት ማብራራት ፤
- የክብርን አስፈላጊነት መናገር፤
- የራስን ደህንነት ማስጠበቂያ ዘዴዎች መዘርዘር፤
- ክብር እንዴት እንደሚገለጽ መለየት፤
- ጉዳት ከሚያደርሱ ነገሮች ራስን መጠበቅ፡፡

## ትምህርት 1. ክብር

### ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገቡ የመማር ብቃት

- የክብርን ምንነት ትገልፃለህ/ጭያሽ፤

### የግንዛቤ ጥያቄ

ክብር ማለት ምን ማለት ነው?

ክብር ማለት ለራስና ለሌሎች ሰዎች አክብሮት መስጠት ነው፡፡

ራስን ማክበር ማለት ደግሞ በራስ መተማመንን ማዳበርና በራስ መኩራትን ያመለክታል፡፡ ሌሎች ሰዎችን ማክበር ማለት ደግሞ ለሰዎች ጥሩ አመለካከት ያለን መሆንና ክብር መስጠትን ያመለክታል፡፡



በራስ መኩራት

## ተግባር 1.

ከዚህ በላይ የቀረበው ምስል ምን እንደሚያመለክት ተናገር/ሪ፡፡

# ቤተሰብ እና ጎረቤታችንን ማገዝ

**የአቶ ዋቆ ቤተሰብ እና ጎረቤታቸው እየተጋገዙ አብረው ይኖራሉ።**



**አቶ ዋቆ ጎጆ ቤት እየሰሩ ነው።**



የእርሳቸው ልጆች ጭቃ በማቡካት ያግዟቸዋል።



የጎረቤት ልጆች ውሃ በመቅዳት ያግዟቸዋል፡፡
ሌንሴ ደግሞ ለእንግዶቹ ቡና እያፈላች ትገኛለች።

## ተግባር 2.

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ስጥ/ጭ፡፡

1. ከላይ የቀረቡት ምስሎች ምን ያመለክታሉ?
2. እናንተ ጎረቤታችሁን በምን በምን ተግባር ታግዛላችሁ?
3. ልጆች ወላጆቻቸውን አለማገዝ ጥሩ ስነምግባር ነው።

   ሀ. እውነት　　　　ለ. ውሸት

4. ጎረቤታችንን ማገዝ አስፈላጊ ነው።

   ሀ. እውነት　　　　ለ. ውሸት

## የግለሰቦችን ልዩነት ማድነቅና ማክበር



ሊባባ



ዱሬሳ

ዱሬሳ፡- እንዴት ነሽ?

ሊባባ፡- እኔ ሰላም ነኝ:: አንተስ ደህናነህ?

ዱሬሳ፡- ስምሽ ማን ይባላል?

ሊባባ፡- ሊባባ እባላለሁ:: ያንተስ?

ዱሬሳ፡- ዱሬሳ እባላለሁ፡፡ሊባባ ልብስሽ በጣም ያምራል።

ሊባባ፡- አመሰግናለሁ፤ ያንተም ያምራል።

ዱሬሳ፡- ደግሞ ደስ የሚል ስም አለሽ።

ሊባባ፡- አመሰግናለሁ፤ በሲዳሞ አፎ ቋንቋ ዱሬሳ ማለት ምን ማለት ነው?

ዱሬሳ፡- ሀብታም ማለት ነው።

ሊባባ፡- ከአፋን ኦሮሞ ጋር አንድ ነው፤በጣም ደስ ይላል።

ዱሬሳ፡- እኔም አመሰግናለሁ! የሁለታችንም ደስ ይላል።

## ተግባር 3.

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

1. ሊባባ እና ዱሬሳ ምን ምን ነበር ያደነቁት?
2. የግል ልዩነቶችን ማክበር አስፈላጊ አይደለም።

   ሀ. እውነት ለ. ውሸት

# ትምህርት 2. የአክብሮት አስፈላጊነት

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃት

- የክብርን አስፈላጊነት ትገልፃለህ/ጭያሽ፣

## የግንዛቤ ጥያቄዎች

ለራሳችን ክብር መስጠት ምን ጥቅም አለው?

ለራሳችን እና ለሌሎች ሰዎች ክብር መስጠት ብዙ ጥቅሞች አሉት።

- ሰውን ማክበር ራስን ማክበር ነው።



- በራስ መተማመን እንዲኖረን ያደርጋል ፤
- የራሳችንን ደካማ እና ጠንካራ ጎን ለይተን ለማወቅ ይረዳል፤
- በራሳችን ለመወሰን አቅም እንዲኖረን ያደርጋል።



በራስ የመተማመን ስሜት ማዳበር

## ተግባር 4.

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

1. ለራሳችን እና ለሌሎች ሰዎች ክብር መስጠት ምን ጥቅም አለው?
2. ሰው እንዲያከብርህ/ሽ ምን ማድረግ አለብህ/ሽ?
3. መከባበር ጓደኝነትን ያጠናክራል።

    ሀ. እውነት ለ. ውሸት

# ትምህርት 3፡ አክብሮትን ማሳያና ማሳደጊያ መንገዶች

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገቡ የመማር ብቃቶች

- ክብርን እንዴት ማሳየት እንደሚቻል ትናገራለህ/ሽ።
- የክብር አሰጣጥ ማጎልበቻ መንገዶችን ትለያለህ/ሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄ

ለቤተሰቦችህ/ሽና ለአዛውንቶች ያለህን/ሽን ክብር እንዴት ታሳያለህ/ሽ?

አክብሮትን የሚናሳይበትና የሚናሳድግባቸው መንገዶች ብዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡

- አዛውንቶችን ማክበር፤
- እናት እና አባትን ማክበር፤





እርስበርስ መከባበር



መረዳዳት





የትምህርት ቤት የደምብ ልብስ መልበስ

ታላቅ እና ታናሽ መከባበር፤



መምህራን ክፍል ውስጥ ሲገቡ ቆሞ በአክብሮት መቀበል



እጅ በማውጣት ጥያቄ መጠየቅ እና መልስ መስጠት



ዕጽዋትን መትከል እና ውሃ ማጠጣት



ከስርቆትና ማጭበርበር መራቅ

## ተግባር 5.

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

1. ለመምህራን ያለህን/ሽን ክብር እንዴት ትገልጻለህ/ጭያለሽ?
2. የራስን ክብር ለማዳበር ምን ምን ተግባራትን ትፈጽማለህ/ሚያለሽ?

# ትምህርት 4. የራስን ደህንነት መጠበቅ

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገቡ የመማር ብቃቶች

- ደህንነታችን ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮችን ትዘረዝራለህ/ሽ።
- ደህንነታችንን የምንጠብቅባቸውን ዘዴዎች ትናገራለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄ

**ደህንነታችንን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?**

ደህንነታችንን መጠበቅ ማለት አደጋን በመፍጠር ጉዳት ሊያደርሱ ከሚችሉ ነገሮች እራስን መጠበቅ ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ:





ስለት ባላቸው ነገሮች ከመጫወት መቆጠብ፡፡



የመኪና መንገድ ስናቋርጥ ግራ እና ቀኝ በመመልከት በጥንቃቄ መሻገር



የግል እና የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ



አስፈሪ እና ጎጂ ከሆኑ ነገሮች መራቅ። ለምሳሌ፡-

በእሳት ከመጫወት መቆጠብ፡፡ የቤትና የዱር እንስሳት እንደ ድመት፣ ቀበሮ፣ ከብቶች እና ሌሎች እንስሳትን ሳያውቁ አለመንካት፡፡

## ተግባር 6. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

1.ደህንነትህ/ሽን የምትጠብቀው/ቂው እንዴት ነው?

2.ደህንነታችንን ለመጠበቅ በሰው ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ ነገሮች መጠንቀቅ አለብን።

ሀ. እውነት ለ. ውሸት

3.ከሚከተሉት ተግባራት ጉዳት ሊያደርስ የሚችለው የቱ ነው? ሀ. በመንገድ ላይ ኳስ መጫወት

ለ. ስለት ባላቸው ነገሮች መጫወት

ሐ. የግል ንጽህናን አለመጠበቅ

መ. ሁሉም መልስ ነው

4.በመኖሪያ ቤታችን አከባቢ ደህንነታችንን ለመጠበቅ ማድረግ ያለብንን ጥንቃቄ ዘርዝር/ሪ፡፡

# ትምህርት 5. የህጻናት ደህንነት መጠበቂያ ዘዴዎች

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገቡ የመማር ብቃት

- ሕፃናት ደህንነታቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ ትዘረዝራለህ/ሽ፣

## የግንዛቤ ጥያቄ

ከቤት ወደ ትምህርት ቤት ስትሄዱ ደህንነትህን/ሽን እንዴት ትጠብቃለህ/ቂያለሽ?

ሕፃናት ደህንነታቸውን በተለያዩ መንገዶች ይጠብቃሉ። ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

- የቤተሰብንና የትላልቅ ሰዎችን ምክር መቀበል





በመንገድ ላይ ኳስ አለመጫወት



ከአቅማቸው ባላይ የሆኑ ስራዎችን አለመስራት





ከምግብ በፊት እና በኋላ እጅን መታጠብ

## ተግባር 7.

ከሚከተሉት ዐረፍተነገሮች የሕፃናት ደህንነት ጥበቃ የሚያሳዩ እና የማያሳዩ ድርጊቶችን ለይታችሁ የ '√' ምልክት ፃፍ/ፊ፡፡

| ተ/ቁ | ተግባራት | ለደህንነት ጥሩ አይደለም | ለደህንነት ጥሩ ነው |
|---|---|---|---|
| 1 | ለብቻ ዋና መዋኘት | | |
| 2 | ከምግብ በፊት እና በኋላ እጅን መታጠብ | | |
| 3 | ስለት ባላቸው መሳሪያዎች መጫወት | | |
| 4 | የቤተሰብን ምክር መስማት | | |
| 5 | እንስሳትን ማባረር እና በእጅ ለመያዝ መሞከር | | |
| 6 | ግራ እና ቀኝ በመመልከት መንገድ መሻገር | | |
| 7 | ከአቅም በላይ የሆነ ስራ መስራት | | |
| 8 | የቤተሰባችንን የስልክ ቁጥር መያዝ | | |
| 9 | የአከባቢያችንን ንጽህና መጠበቅ | | |
| 10 | ሰውን መሳደብ | | |

## ማጠቃለያ

ግብረገብ ለፈጣሪ፣ ለሰው ልጅ እና ለተፈጥሮ አክብሮት መስጠትን ያመለክታል። በፈጣሪ እና በተፈጥሮ፣ በሰው እና በተፈጥሮ እንዲሁም በሰው እና በሰው መካከል ያለው ግንኙነት የሚመራው በግብረገብ ነው። ግብረገብ ያለው ሰው አክብሮት አለው። አክብሮት ያለው ሰው ደግሞ ታማኝነት ይኖረዋል።

ልጆች ታላላቆቻቸውንና ቤተሰብን በማክበር፣ ከማጭበርበር እና ከስርቆት በመራቅ ያላቸውን አክብሮት ማሳየት እና ማጎልበት ይችላሉ። እንዲሁም መልካም ጸባይን መጎናጸፍ የቤተሰብን እና የመምህራንን ምክር መቀበልና የትምህርትቤት ሕገ ደንብ የማክበር ልምድ ማሳደግ ይችላሉ።

ደህንነታችንን ለመጠበቅ አደጋ ሊያደርሱ ከሚችሉ ነገሮች ሁሉ መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው። ይህም ስለት ባላቸው ነገሮች አለመጫወት፣ግራ እና ቀኛቸውን በመመልከት መንገድ ማቋረጥ፣ የግል እና የአከባቢ ንጽህናን መጠበቅ እንዲሁም ከሚያስፈሩ ነገሮች መራቅ ያስፈልጋል።

# የክለሳ ጥያቄዎች

የሚከተሉት ጥያቄዎች  የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ "ውሸት" በማለት መልስ/ሽ::

1. ቤተሰባችንንና ወንድሞቻችንን ማክበር አስፈላጊ አይደለም።
2. ልዩነትን ማክበር ከማህበረሰባችን ግብረገብ ማሳያ ውስጥ አንዱ ነው።
3. ራሳችንን ማክበር በራስ መተማመናችንን ያሳድጋል።
4. መጸዳጃ ቤትን ከተጠቀምን በኋላ እጃችንን መታጠብ አለብን።
5. ለራሳችን ክብር መስጠት ጠንካራ እና ደካማ ጎናችንን ለማወቅ ያግዘናል።

II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ።

1. የክብር ማሳያ እና ማጎልበቻ መንገድ ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. የትምህርት ቤት ደንቦችን ማክበር

   ለ. ለመማሪያ ክፍል ደንብ ክብር አለመስጠት

   ሐ. የግል ልዩነቶችን ማድነቅ

   መ. አንድ ሰው ለሚወደው ነገርክብር መስጠት

2. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ለራስ ክብር መስጠት  ሐ. ሌሎችን ሰዎች ማክበር

   ለ.  ደህንነታችንን መጠበቅ  መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

3. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. አረጋውያንን ማክበር

ለ. ወንድሞቻችንን ማክበር

ሐ. ጎረቤቶቻችንን አለማክበር

መ. ጓደኞቻችንን ማክበር

4. ከሚከተሉት ደህንነታችንን ለመጠበቅ የሚረዳን የቱ ነው?

ሀ. ለብቻ የመኪና መንገድ አለማቋረጥ

ለ. የቤተሰብን ስልክ ቁጥር ማወቅ

ሐ. ስለደህንነት ከቤተሰብ ጋር መወያየት

መ. ሁሉም መልስ ነው

5. ለሕጻናት ደህንነት ጥበቃ አስፈላጊ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. በመንገድ ላይ ኳስ መጫወት

ለ. የጥርስ ብሩሽን ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ መጠቀም

ሐ. የወላጅ፣የታላላቆችንና የመምህራንን ምክር መስማት

መ. ግራ እና ቀኝ ሳያዩ መንገድን በፍጥነት ማቋረጥ

# ምዕራፍ 2

# እውነተኛነት እና ታማኝነት

## የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

- የእውነተኛነት እና ታማኝነት ምንነት መግለጽ፤
- የእውተኛነት እና የታማኝነት አመላካቾችን መናገር።

## ትምህርት 1. የእውነተኛነት እና ታማኝነት ምንነት

### ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃት

- የእውተኛነትን እና የታማኝነትን ምንነት ትገልጻለህ/ሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄ

እውነት መናገር ምን ፋይዳ አለው?

እውነት በኦሮሞ ባህል ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው። እውነት የፈጣሪ ልጅ ነው ተብሎ ይታመናል። ፈጣሪ እውነትን ይወዳል። ሰው ደግሞ በእውነት ይኖራል፤ አይዋሽም፡፡ ስለዚህ ልጆችም እውነት እንጂ ውሸት መናገር የለባቸውም። እውነት የሚናገር ሰው ደግሞ ታማኝ ስለሆነ በሁሉም ሰዎች ዘንድ ይወደዳል።

## ተግባር 1.

1. እውነት የሚናገር ሰው በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅነት ያተርፋል፡፡

   ሀ. እውነት ለ. ውሸት

2. ልጆች እውነት ቢናገሩ መልካም ነው፡፡

   ሀ. እውነት ለ. ውሸት

## ትምህርት 2. የእውነተኛነት እና የታማኝነት ማሳያዎች

### ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገቡ የመማር ብቃቶች

- የእውነተኛነት እና የታማኝነት ማሳያዎችን ትዘረዝራለህ/ሽ፤
- እውነት መናገር ያለውን ጥቅም ትናገራለህ/ሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄ

እውነተኛነት እና ታማኝነት በምን በምን ተግባራት ሊገለጹ ይችላሉ?

እውነተኛነት እና ታማኝነት በተለያዩ ሁኔታዎች ሊገለጹ ይችላሉ። እነዚህም፡- አለመዋሸት፣ ቃልኪዳንን መጠበቅ፣ ስርቆትንና ማታለልን መጥላት፣ ሁልጊዜ እውነት መናገር እና የመሳሰሉት ናቸው።

እውነትን የሚናገሩ ልጆች በእናት እና በአባታቸው ዘንድ ይወደዳሉ። እንዲሁም በጓደኞቻቸው፣ በመምህራን እና በጎረቤታቸው በጣም ይወደዳሉ።

ፈጣሪም ይወዳቸዋል፡፡ ስለዚህ፣ ልጆች በተቻለ መጠን ከእውነት በስተቀር ውሸት መናገር የለባቸውም፡፡

## ተግባር 2. ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ።

1. እውነት የሚናገር እና ታማኝ የሆነ ሰው ምን ያገኛል?
   - ሀ. የእናት እና የአባት ፍቅር
   - ለ. የመምህራን ፍቅር
   - ሐ. የአባት በረከት
   - መ. ሁሉም መልስ ነው

2. እውነተኛነት እና ታማኝነትን የማይገልጽ የቱ ነው?
   - ሀ. አለመዋሸት
   - ለ. ቃልኪዳንን ማክበር
   - ሐ. ማጭበርበር
   - መ. ከሌብነት መራቅ

3. ከሚከተሉት አባባሎች እውነትን የሚገልጽ የቱ ነው?
   - ሀ. እውነት ትቀጥናለች እንጂ አትበጠስም
   - ለ. በእውነት የምታለቅስ ዓይን እንባ አታጣም
   - ሐ. እውነት ተናግሮ በመሸበት ማደር
   - መ. ሁሉም መልስ ነው

# ዝንጀሮ እና ዓይጥ

በድሮ ጊዜ አንድ ሰው ከዝንጀሮ እና ከዓይጥ ጋር ይኖር ነበር።



ሰውየው ከቤት ሲወጣ ዓይጧ ተደብቃ ጤፉን ከጎተራ ውስጥ በልታ ጨረሰች።



አንድ ቀን ሰውዬው ጤፉን ሊወስድ ሲሄድ ከጎተራ ውስጥ አጣ።



ከዚያም ዝንጀሮ እና ዓይጥን ጠርቶ “ጤፌን ማን እንደበላው ንገሩኝ! ማንነው የበላው? የማትናገሩ ከሆነ እገላችኋለሁ!::” አላቸው። ሁለቱም አልበላንም ብለው ማሉ። ሰውየውም የሚያረገውን አጣ።



ከዚያም ዓይጧ እጅ በማውጣት ሳር ውስጥ አስገባን እና እሳት ለኩስብን። እውነት ያለው ይትረፍ። ውሸታሙ ግን ተቃጥሎ ይሙት አለች።



በስምምነታቸው መሰረት ሰውየው ሳር ውስጥ አስቀምጦአቸው እሳት ለኮሰባቸው። ዓይጧም ተደብቃ ወደ ቆፈረችው ጉድጓድ እየሮጠች ገባች። ዝንጀሮው ደግሞ የሚያረገውን አጣ። ሰማይ እያየ ማልቀስ ጀመረ።



በመጨረሻም ከባድ ዝናብ ዘንቦ እሳቱን አጠፋው።



ከዚያም በኋላ ጎርፍ ጉድጓዱ ውስጥ ገብቶ ዓይጧን ገደላት።በዚህ መልኩ ዝንጀሮ እውነት ስላለው ከሞት ተረፈ፤ ዓይጧ ደግሞ በማጭበርበሯ ሞተች ይባላል።

## ተግባር 3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

1. ዓይጧ በእሳት ተቃጥላ ሞተች።
   ሀ. እውነት ለ. ውሸት
2. ዝንጀሮ እውነት ስላለው ከሞት ተረፈ።
   ሀ. እውነት ለ.ውሸት
3. ዓይጥ እውነት ስላሌላት ሞተች።
   ሀ. እውነት ለ.ውሸት
4. እውነት ያለው ማን ነው ብላችው ታስባላችሁ? ለምን?

# ትምህርት 3. ቃልኪዳንን ማክበር

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃት

- ቃልኪዳን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትለያለህ/ሽ፡፡
- ቃልኪዳንን ማክበር ያለው ፋይዳ ትገልጻለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄ

**አንድን ነገር እሰራለሁ ብለህ/ሽ ለወላጆችህ/ሽ ቃል ገብተህ/ሽ ታውቃለህ/ሽ?**

ቃልኪዳን መሀላ ነው። አልዋሽም ብለው በመሃላ ቃል መግባት ነው። የገቡትን ቃል ማፍረስ ግን ግብረገብነትን መጣስ ነው። ቃልኪዳንን ማፍረስ ሰውን ያዋርዳል። ስለዚህ እሰራለሁ ብለን ለቤተሰቦቻችን፣ ለጓደኞቻችን እና ለአስተማሪዎቻችን የገባነውን ቃልኪዳን ማክበር ይገባናል።

## ቀበሮና ፍየል



ከዕለታት አንድ ቀን ቀበሮ ምግብ ፍለጋ እየዞረ ሳለ ጉድጓድ ውስጥ ወድቆ መውጣት አቃተው። በዚህ ወቅት አንድ አውራ ፍየል ውሃ ሊጠጣ ፈልጎ መጣና ቀበሮውን ጉድጓድ ውስጥ አየው።

“እዚህ ውስጥ ምን እየሰራህ ነው?” ሲል ቀበሮውን ጠየቀ። ቀበሮውም “ውሃ እየጠጣሁ ነው፤ አንተም ና ጠጣ::” ብሎ አታለለው።



ፍየሉም እውነት መስሎት ዘሎ ገባ፣



ከዚያም መውጣት እንዳቃተው ነገረው፡፡



ከዚያም በኋላ ቀበሮው ፍየሉን “ሁለቱን እጆችህን አንስተህ መሬቱ ላይ ርገጥ፤ እኔ አንተ ላይ ቆሜ እወጣለሁ። እኔም በተራዬ እጆችህን ይዤ አወጣሃለሁ::” አለው። ፍየሉም “እንደገና ልታታልለኝ ነው አይደለም?” አለው። ቀበሮውም “አይደለም፣አላታልልህም::” በማለት ቃል ገባለት። ወዲያው ፍየሉም ሁለቱንም እጆቹን ሲያነሳ በላዩ ረግጦ ከጉድጓዱ ወጣ።



ቀበሮው ከጉድጓዱ እንደወጣ የገባውን ቃልኪዳን በማፍረስ ጥሎ ሄደ።



እየሄደ እያለ ፍየሉን ፍለጋ ከመጡ ሰዎች ጋር ተገናኘ። እነሱም “ይህ ቀበሮ ፍየላችንን በልቶ ይሆናል::” ብለው ከከበቡት በኋላ ገደሉት።



በመጨረሻም ፍየሉ ከጉድጓድ ውስጥ ሲጮህ ድምጹን ሰምተው አውጥተው ወስደው ወደቤታቸው ገቡ። በዚህ ሁኔታ ቀበሮው የገባውን ቃልኪዳን በማፍረሱ ምክንያት ተጎድቶ ሞተ ይባላል።



## ተግባር 4. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ።

1. ቃልኪዳኑን ያፈረሰ ማነው?
   - ሀ. ሰዎች
   - ለ. ፍየል
   - ሐ. ቀበሮ
2. ቀበሮው እንዲሞት ምክንያት የሆነው ዬቱ ነው?
   - ሀ. ስለተራበ
   - ለ. ቃልኪዳን ስላፈረሰ
   - ሐ. ስለደከመው
3. ቃልኪዳንን የሚጠብቅ __________፡፡
   - ሀ. እውነት የለውም
   - ለ. ታማኝ ነው
   - ሐ. አክብሮት የለውም
4. ቃልኪዳንን ማፍረስ ትክክል አይደለም።
   - ሀ. እውነት
   - ለ. ውሸት
5. ከዚህ ታሪክ ውስጥ ያስደሰተህ/ሽን ነገር ተናገር/ሪ፡፡
6. ከዚህ ታሪክ ምን ተማርክ/ሽ?

# ትምህርት 4. መስረቅ እና ማጭበርበርን መጥላት

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃት

- መስረቅ እና ማጭበርበር የሚያስከትለውን ጉዳት ትለያለህ/ሽ፡፡

## የግንዛቤ ጥያቄ

**የሰውን ንብረት መስረቅ እና ማታለል ምን ጉዳት አለው?**

የሰውን ንብረት የሚሰርቅ ሰው እርጉም ነው ተብሎ ይታመናል። የተረገመ ሰው ደግሞ እንደማይሳካለት ይታሰባል። ማታለል እና መዋሸት እውነትን መደበቅ ነው። ሰውን የሚያታልል ሰው አይታመንም። እንዲሁም ስርቆትና ማታለል በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ታማኝነትን ያሳጣል፡፡ ታማኝነት ማጣት ደግሞ ግብረገብነትን መጣስ ስለሆነ ነውር ነው። ስለዚህ ከመስረቅ እና ከማታለል መራቅ አለብን።

## ተግባር 5. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

1. የሰውን ንብረት የሚሰርቅ ሰው__________ ነው።
   ሀ. ክቡር ለ. እርጉም
2. ሰውን የሚያታልል ሰው__________ የለውም።
   ሀ. ታማኝነት ለ. ኃጥያት
3. ሌብነት እና ማታለል ምግባረ ብልሹነትን ያመለክታሉ፡፡
   ሀ. ውሸት ለ. እውነት
4. ታማኝነትን ማጣት __________ መጣስ ነው።
   ሀ. ግብረገብነትን ለ. እርግማንን
5. የተረገመ ሰው __________።
   ሀ. ይቀናዋል ለ. አይሳካለትም

## ማጠቃለያ

እውነት መናገር እና ታማኝ መሆን ብዙ ጥቅሞች አሉት። እውነትን የሚናገሩ ልጆች በወላጆቻቸው፣ በጓደኞቻቸው፣ በመምህራን እና በጎረቤታቸው በጣም ይወደዳሉ። መዋሸት፣ማታለል እና መስረቅ ግን በሰዎች ዘንድ የተጠላ እና የማይወደድ ያደርጋል።

እንዲሁም ቃልኪዳንን ማፍረስ፣ መዋሸት እና መስረቅ ግብረገብነትን መጣስ ነው። ግብረገብነትን ለመጠበቅ እውነተኛ እና ታማኝ መሆን ይጠይቃል። ቃል ኪዳን ከማፍረስ፣ ከመዋሸት እና ከስርቆት መራቅ ያስፈልጋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

I. የሚከተሉት ጥያቄዎች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ "እውነት" ካልሆነ ግን "ውሸት" በማለት መልስ/ሺ።

1. እኛ ከሰዎች ክብርን ለማግኘት ለሌሎች ክብር መስጠት አያስፈልግም።
2. እውነትን መናገር እና ታማኝ መሆን ግብረገብነትን ያጎናጽፋል።
3. ለአንድ ሰው የገባነውን ቃል መጠበቅ አለብን።
4. ታማኝነት በመስረቅ፣ በመዋሸት እና በማታለል ይገለጻል።

## II. ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ።

1. ከሚከተሉት አማራጮች ግብረገብነትን የማያሳይ የቱ ነው?

   ሀ. ሕጎችን ማክብር

   ለ. ለሰው መልካም ማሰብ

   ሐ. ውሸት መናገር

   መ. እውነት መናገር

2. ከሚከተሉት አማራጮች ታማኝነትን የሚያሳይ የቱ ነው?

   ሀ. እውነትን መናገር

   ለ. ስርቆትን እና ማታለልን መጥላት

   ሐ. ትክክለኛውን ነገር ማድረግ

   መ. ሁሉም መልስ ነው

3. ልጆች ታማኝ መሆን ያለባቸው ለማን ነው?

   ሀ. ለቤተሰብ

   ለ. ለጓደኛ

   ሐ. ለመምህራን            መ. ሁሉም

4. ከሚከተሉት ታማኝነትን ከማጣት የሚመጣ ዬቱ ነው?

   ሀ. በወላጆች መረገም

   ለ. በጓደኞች መወደድ

   ሐ. በሰዎች መከበር

   መ. በወላጆች መመረቅ

# ምዕራፍ 3

# ፍትህ

## የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

- የፍትህ እና ፍትሃዊነት ምንነትን መግለጽ፣
- የፍትህ እና ፍትሃዊነት አስፈላጊነት መናገር፣
- ከፍትህ ጉድለት የሚመጣን ጉዳት መለየት ናቸው።

## ትምህርት 1. የፍትህ ምንነት

### ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገቡ የመማር ብቃት

- የፍትህን ምንነት ትለያለህ/ሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄ

የራስ ያልሆነን ነገር ከመሬት ብታገኝ/ኚ ምን ታደርጋለህ/ሽ?

እውነት መናገር ፍትህ ነው። የሰው የሆነውን ለባለቤቱ መልሶ መስጠት ፍትህ ነው። ፍትህ ሰዎችን ሳያበላልጡ በእኩልነት ማየትንም ያካትታል። ሁሉንም ሰው ያለ አድልዎ እኩል ማስተናገድ እንደ ፍትህ ሊታይ ይችላል፡፡ ፍትህ በሌለበት ቦታ እውነት አይኖርም። እውነት በሌለበት ቦታ ደግሞ ፍቅር የለም።

ስለዚህ ፍትህን ማስፈን ለሰላም ግንባታ ወሳኝ ሚና አለው።

## ሶስቱ ጓደኞች



ከዕለታት በአንድ ቀን ሶስት ጓደኞች መንገድ ላይ ሲሄዱ መሸባቸው። ወደ አንድ ቤት ጎራ ብለው "አሳድሩን" አሉ። የቤቱ ባለቤትም "ቤት የፈጣሪ ነው እደሩ" አሉ። ሰዎቹም በለሊት ተነስተው ከብቶቻቸውን ዘርፈው ጠፉ፡፡



ሶስቱም ሌቦች ቀኑን ሙሉ ተጉዘው ስለራባቸው ሁለት ሰዎች ምግብ አንድ ሰው ግን ውሃ ለመፈለግ ተስማሙ። ከዚያም በኋላ ሁለቱ ሰዎች አንዱን ሰው ገድለው በሬዎቹን ለሁለት ለመካፈል

ወሰኑ።



አንደኛውም ሁለቱን ገድሎ በሬዎቹን ለመውሰድ አሰበ። ስለዚህ ካገኘው ውሃ ጠጥቶ ለእነሱ ደግሞ የሚገድል መርዝ ጨምሮበት መጣ።





ልክ ሰውየው ሲመጣ ውሃውን ተቀብለው እሱን ደግሞ ደብድበው ገደሉት።



ከዚያም ሁለቱ ውሃውን ጠጥተው ታመው ሞቱ።



በሬዎቹ የተሰረቁበት ሰው ደግሞ በሬዎቹን ሲፈልግ የሁለቱን ሰዎች ሬሳ አይቶ ደነገጠ። በእነሱ አጠገብ ደግሞ ዞር ሲል በሬዎቹን አገኘ። በዚህ መልኩ የሰውን ሃቅ ለመውሰድ የሞከሩ ሰዎች አልቀው የበሬዎቹ ባለቤት ሃቁን ይዞ ወደቤቱ ተመልሶ ገባ ይባላል።



## ተግባር 1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

1) የሰውን ሀቅ መስረቅ ሰውን ለችግር አያጋልጥም።

ሀ. እውነት ለ. ውሸት

2) የቤቱ ባለቤት ሀቅ ስላለው ንብረቱን አገኘ።

ሀ. እውነት ለ. ውሸት

3) እንግዳን ማሳደር የኦሮሞ ባህል ነው።

ሀ. እውነት ለ. ውሸት

4) ከዚህ ታሪክ ምን ተማርክ/ሽ?

# አለሙ እና ዋሪዮ

አንድ ቀን ገነሜ በማለዳ ተነስታ ወደ አንድ ቦታ ስትሄድ አለሙ እና ዋሪዮ መንገድ ላይ ሲጣሉ አይታ "ለምንድን ነው የምትጣሉት?" ብላ ጠየቀቻቸው። እነሱም ከመሬት ባገኙት ገንዘብ ላይ እየተጣሉ እንደሆነ ነገሯት።



እሷም "ከመሬት ያገኛችሁትን ገንዘብ ለባለቤቱ መልሱ::" ብላ መክራቸው አልፋ ሄደች።



በዚህ መሀል ገንዘቡ የጠፋበት ሰው መጥቶ "የሆነ ገንዘብ አግኝታችኋል?" ብሎ ጠየቃቸው። ሁለቱም ልጆች ገንዘቡ የእሱ መሆኑን ከተረዱ በኋላ ገንዘቡን ሰጡት። የገንዘቡም ባለቤት ባደረጉት ነገር ተደስቶ ስሞ እና መርቋቸው ሄደ።



ልጆቹም ተደስተው እየሮጡ ወደቤታቸው ሄዱ።

## ተግባር 2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

1. ገነሜ የሰውን ሃቅ አትወስድም።

   ሀ. እውነት

   ለ. ውሸት

2. አለሙ እና ዋርዮ ለምን ተደሰቱ?

   ሀ. ገንዘብ ስላገኙ

   ለ. ምርቃት ስላገኙ

   ሐ. ስለተጣሉ

3. በወላጆች የሚመረቅ ሰው ያድጋል።

   ሀ. እውነት

   ለ.ውሸት

4. ከዚህ ታሪክ ምን ተማርክ/ሽ?

# ትምህርት 2. ፍትሃዊነት

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገቡ የመማር ብቃት

- የፍትሃዊነትን ምንነት ትለያለህ/ሽ፣

## የግንዛቤ ጥያቄ

ሁሉንም ሰው እኩል ማክበር አግባብ ነው? ለምን?

ፍትሃዊነት ሁሉንም ሰው እኩል ማክበር እና በታማኝነት ማገልገል ነው። ይህም ለሁሉም ሰው እኩል ዕድል መስጠትን ያመለክታል። ስለዚህ በተለያዩ አገልግሎቶች ውስጥ ሰዎች እንዳይጎዱ ማድረግ አለብን።

### ተግባር 3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

1. ፍትሃዊነት ሁሉንም ሰው እኩል ማገልገል ነው።

   ሀ. እውነት ለ. ውሸት

2. ለሰው መልካም ነገር ማሰብ ፍትሃዊነት ነው።

   ሀ. እውነት ለ. ውሸት

3. ፍትሃዊነት አዛውንቶችን ብቻ ማክበር ነው።

   ሀ. እውነት ለ. ውሸት

## ማጠቃለያ

ፍትህ እና ፍትሃዊነት ለሰዎች በአብሮነት ለመኖር አስፈላጊ ነው። ፍትህ እውነት መናገር እና የሰው ሃቅ ወደ እኛ እንዳያልፍ መጠንቀቅ ነው። ፍትሃዊነት ደግሞ ሰዎችን እንደ አቅም እና ችሎታቸው እኩል ማገልገል ነው። ከዚህ በተጨማሪ ለሰዎች ሁሉ እኩል አክብሮት መስጠት እና በታማኝነት ማገልገል ነው። እንዲሁም ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ድጋፍ ማድረግ ነው።

## የክለሳ ጥያቄዎች

I. የሚከተሉት ጥያቄዎች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ "እውነት" የተሳሳተ ከሆነ "ውሸት" በማለት መልስ/ሽ፡፡

1. ለፍትህ የሚቆም ሰው ሊበረታታ ይገባል።
2. ፍትሃዊነት ለሰዎች ክብር መስጠትን ያጠቃልላል።
3. ፍትሃዊነት ሁሉንም በእኩል ማገልገል ነው፡፡
4. ፍትሃዊነት እውነት መናገርን አያጠቃልልም።
5. መልካም አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች የሌሎችን ሰዎች ችግር ይረዳሉ፡፡

## II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ።

1. ከሚከተሉት የመልካም ሰው ባሕርይ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ሁሉንም ሰው መውደድ

   ለ. የሌሎችን አስተያየት መቀበል

   ሐ. መድልዎ አለማድረግ

   መ. ሁሉም መልስ ነው

2. ሰዎች እኩል ዕድል ካገኙ ምን ይሆናሉ?

   ሀ. እርስ በርስ ይተሳሰባሉ

   ለ. አብሮ መስራት ይመርጣሉ

   መ. ሁሉም መልስ ነው

   ሐ. በራሳቸው ይደሰታሉ

3. የመልካም ሰው ባሕርይ ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ለሌሎች ቅድሚያ መስጠት

   ለ. በምክንያት አለማመን

   ሐ. የተቸገሩትን መርዳት

   መ. ሰውን ማዳመጥ

4. የፍትሃዊነት መኖር ለምን ያስፈልጋል?

   ሀ. ለመተማመን

   ለ. ችግሮችን ለመፍታት

   ሐ. አብሮ ለመስራት መ. ሁሉም መልስ ነው።

# ምዕራፍ 4

# መልካም ማህበራዊ ግንኙነት

## የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

- የመልካም ግንኙነትን ምንነት ትገልጻለህ/ጫለሽ፣
- መልካም ግንኙነቶችን ሊያጎለብቱ የሚችሉ ነገሮችን ትለያለህ/ሽ፣
- መልካም ጓደኝነትን የሚጎዱ ነገሮችን ትለያለህ/ሽ።

## ትምህርት 1. ጓደኝነት

### ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃት

- ጓደኝነት የሚገለፅባቸውን መንገዶች ትለያለህ/ሽ፣

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. መልካም ማህበራዊ ግንኙነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ጓደኝነት ምንድን ነው?
3. ጓደኝነት በምን በምን ይገለጻል?

መልካም ማህበራዊ ግንኙነት ማለት እውነተኛ ጓደኝነትና በጋራ ፍላጎታችን ላይ በመመስረት ተደጋግፎ የመኖር ግንኙነት ነው፡፡ በመሆኑም መልካም ማህበራዊ ግንኙነትን ከሚያመለክቱ ነገሮች ጓደኝነት አንዱ ነው፡፡

ጓደኝነት በሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ግንኙነት ሲሆን ይህ ጓዳኝነትም በመከባበር፣ በመደማመጥ፣ በመዋደድ፣ አብሮ በመሥራት እና አብሮ በመጫወት ይገለጻል። እነዚህ ተግባራት መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር ያደርጋሉ። ለምሳሌ ቀጥሎ የቀረበው የልጆች ጫወታ ጓደኝነትን ያጠናክራል፡፡





| ጠያቂ | መልስ ሰጪ |
| --- | --- |
| ሁርዬ | ወይዬ |
| ወንድምሽ የትሄደ? | ዘመቻ |
| ምን ለብሶ? | ነጠላ |
| ውሃ ከየት ቀዳሽ? | ከምንጩ |
| ማን አሸከመሽ? | አለሚቱ |

ኧረ ተይኝ ተይኝ አለሚቱ ... ኧረ ተይኝ ተይኝ አለሚቱ...

## ተግባር 1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ፡፡

1. ጓደኝነት ግንኙነትን ያጠናክራል፡
   ሀ. እውነት ለ. ውሸት
2. የራሳችንን ጓደኛ መውደድ አስፈላጊ ነው።
   ሀ. እውነት ለ. ውሸት
3. ጓደኝነትን የሚያጠናክረው ዬቱ ነው?
   ሀ. እገዛ የሚፈልጉትን መርዳት
   ለ. አብሮ መጫወት
   ሐ. እርስ በርስ መተማመን
   መ. ሁሉም መልስ ነው።
4. ግንኙነታችሁን ለማጠናከር በትምህርት ቤት ውስጥ ምን ምን እንደምታደርጉ ዘርዝሩ።



ተማሪዎች ትምህርት ቤት ውስጥ አብረው ሲጫወቱ የሚያሳይ ምስል ይግባ



ተማሪዎች አብረው እየተጫወቱ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ የሚያሳይ ምስል ይግባ

# ትምህርት 2. መረዳዳት

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃት

- መረዳዳት ግንኙነትን ከሚያጠነክሩ ነገሮች አንዱ እንደሆነ ትረዳለህ/ጃለሽ፡፡

## የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. መረዳዳት ምንድን ነው?
2. የቤት ሥራችሁን ስትሰሩ የሚረዳችሁ ሰው አለ?
3. ምን በማድረግ ነው የሚረዱችሁ?

መረዳዳት ጥሩ ማህበራዊ ግንኙነት እንዲኖር የሚያደርግ ተግባር ሲሆን አንድን ሰው የከበደው ሰራ እንዲቀለው/ላት ያደርጋል፡፡ ሰዎች በሥራ ላይ በሐሳብም ሆነ በጉልበት ይረዳዳሉ። ሁሉም የተስማሙበት ነገር ላይ በአግባቡ ሥራቸውን ያከናውናሉ። ተማሪዎችም እንደዚሁ በመ፣ዳዳት ብዙ ነገሮችን አብረው ይሰራሉ፡፡ ለምሳሌ በመምህራኖቻቸው የሚሰጧቸውን የቡድን ስራ በመረዳዳት ይሰራሉ። ይህ ደግሞ ማህበራዊ ግንኙነቶችን ለማጠናከር ይረዳል፡፡



ተማሪዎች ተባብረው መማሪያ ክፍላቸውን ያጸዳሉ፡፡



የቤተሰብ አባል  እርስ በርስ በመረዳዳት ዛፎችን ሲንከባከቡ



ማህበረሰቡ ተባብሮ የእርከን ስራ ሲሰራ

# አዞ እና ሦስት ወንድማማቾች



የሦስቱን ታሪክ የሚያሳይ ሥዕል ይግባ

በአንድ ወቅት ሦስት ወንድማማቾች አብረው ይኖሩ ነበር። አንዱ ዋሽንት መንፋት ይችላል፤ሌላው ቀስት መወርወር ይችላል፣ሦስተኛው ደግሞ ውሃ መዋኘት ይችል ነበር፡፡ ሦስቱም እኔ የተሻልኩ ነኝ በማለት ይፎካከራሉ።



አንድ ቀን ከእህታቸው ጋር በመሆን በወንዝ ዳር ልብስ ሲያጥቡ አዞ ከውሃ ወጥቶ እህታቸውን ወስዶ ወደ ውሃው ገባ። እነሱም ደንግጠው እህታቸውን ለማዳን የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ጀመሩ።



ዋሽንት መንፋት የሚችለው የተሰማውን ሃዘን ለመግለጽ ዋሽንቱን መንፋት ጀመረ፡፡ ከዚያም አዞው ከውሃው ውስጥ ብቅ ብሎ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብሎ የዋሽንቱን ድምፅ መስማት ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ ቀስት መወርወር የሚችለው በቀስት ጭንቅላቱን አለውና ገደለው፡፡ከዚያ በኋላ ዋና የሚችለው ደግሞ ወደ ውሃው ገብቶ እየዋኘ እህታቸውን ፈልጎ አወጣት፡፡



በዚሁ መሠረት ሦስቱም ወንድማማቾች ባላቸው ችሎታ በመረዳዳት እህታቸውን ከሞት ለማዳን ችለዋል። በመጨረሻም እኔ እሻላለው የሚለው ሐሳብ ስህተት መሆኑን በመረዳት በደስታ ወደ ቤታቸው ገቡ ይባላል።

## ተግባር 2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ፡፡

1. ሦስቱም ወንድማማቾች የተለያየ ችሎታቸውን ተጠቅመውበታል።
   ሀ. እውነት
   ለ. ውሸት
2. እህታቸውን ለማዳን የተሳተፈው ማን ነው?
   ሀ. ዋሽንት የሚነፋው
   ለ. ውሃ ዋና የሚችለው
   ሐ. ቀስተኛው
   መ. ሁሉም መልስ ነው።
3. ከቀረበው ታሪክ ምን ተማርክ/ሽ?
4. ከዚህ ታሪክ ውስጥ ያስደሰተህ/ሽ ነገር ምን አለ?

# ትምህርት 3. ጓደኝነትን የሚጎዱ ነገሮች

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃት

- ጓደኝነትን የሚጎዱ ነገሮች ትዘረዝራለህ/ሽ፣

## የግንዛቤ ጥያቄ

ከጓደኞችህ/ሽ ጋር ተጣልተህ/ሽ ታውቃለህ/ቂያለሽ? ለምን?

ጓደኝነትን የሚጎዱ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

- ግብረገብነትን አለማክበር
- መናናቅ
- የመጫወቻ ዕቃዎችን መቀማማት
- በሰልፍ ላይ በኃይል መገፋፋት
- ራስ ወዳድነት
- አለመተማመን
- መጠላላት
- መሰራረቅ
- መወሻሸት

# ጃራና ጓደኛው

ጃራ የሁለተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ አንድ ቀን የጓደኛውን ብዕር ደብቆ ሠርቆ ገባ፡፡ ጓደኛውም ፈልጎ አጥቶ ጃራ እንደ ወሰደበት በመገመት ትቶ ሄደ። በማግስቱ የጓደኛውን መጽሐፍ ተውሶ ገጾቹን ቀዳዶ መለሰለት። ጓደኛውም በድርጊቱ በጣም ተናዶ ለመምህሩ ተናግሮ አስቀጣው። ጃራም ከዚያን ቀን ጀምሮ የቅርብ ጓደኛ አጣ።

## ተግባር 3.

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጥ/ጭ፡፡

1. ጃራ ለምን ጓደኛ አጣ?
2. የጃራ ድርጊት ትክክል ነው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ሽ? ለምን?
3. ጓደኝነትን የሚጎዳ ድርጊት የቱ ነው?

   ሀ. እርስ በርስ መጣላት

   ለ. መወሻሸት

   ሐ. አለመከባበር

   መ. ሁሉም መልስ ነው።

# ማጠቃለያ

መልካም የማህበራዊ ግንኙነቶች እንዲፈጠሩ ከሚያደርጉ ነገሮች ውስጥ ጓደኝነትና መረዳዳት ዋነኞቹ ናቸው፡፡ ጓደኝነት በመዋደድ፣በመከባበርና አብረው በመጫወት ሊገለጽ ይችላል፡፡ መረዳዳት ደግሞ ባለን ጉልበትና አቅም አብሮ መሥራት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሌላ በኩል መልካም ማህበራዊ ግንኙነት እንዲፈጠር ይረዳል፡፡ መልካም የማህበራዊ ግንኙነትን ለማስቀጠል ጥሩ ግንኙነትን ከሚጎዱ ነገሮች መቆጠብ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ ድርጊቶች መናናቅ፣መወሻሸትና ከራስ ወዳድነት መራቅ ናቸው፡፡

# የክለሳ ጥያቄዎች

**I. የሚከተሉት ጥያቄዎች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ “እውነት” የተሳሳተ ከሆነ ደግሞ “ውሸት” በማለት መልስ/ሽ፡፡**

1. ጓደኛ ማክበር አስፈላጊ አይደለም፡፡
2. ራስ ወዳድነት የጓደኝነትን ግንኙነት ይጎዳል፡፡
3. መረዳዳት ማህበራዊ ግንኙነትን ያጎለብታል፡፡

**II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ**

1. ጓደኝነትን የማይጎዳ ድርጊት የቱ ነው?

   ሀ. መዋደድ

   ለ. አለመዋሸት

   ሐ. መከባበር

   መ. ሁሉም መልስ ነው

2. የመረዳዳት ጥቅም የማያሳየው የቱ ነው?

   ሀ. በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ማጠናከር

   ለ. ግጭትን መቀነስ

   ሐ. መዋደድን መቀነስ

   መ. መልስ አልተሰጠም

3. ጓደኝነትን የሚያጠናክር የቱ ነው?

   ሀ. ያላቸውን ማካፈል

   ለ. አብሮ መጫወት

   ሐ. መረዳዳት

   መ. ሁሉም መልስ ነው

# ምዕራፍ 5

# ለጋራ ንብረት መጠንቀቅ

## የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

- የጋራ ንብረትን መለየት፤
- የጋራ ንብረትን ምንነት መግለጽ፤
- የጋራ ጥቅም እንቅፋቶችን መለየት።

## ትምህርት 1. የጋራ ንብረት ምንነት

### ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃት

- የጋራ ንብረት የሆኑ ነገሮችን ትለያለህ/ሽ።

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

- አንድ ማህበረሰብ በጋራ የሚጠቀምባቸውን ነገሮች ዘርዝር/ሪ፡፡
- ከዚህ በታች የቀረቡት ምስሎች ምንን ያሳየሉ?

## የጋራ ንብረት ምንነት

አንድ ማህበረሰብ በጋራ የሚጠቀሙባቸው ነገሮች በሙሉ የጋራ ንብረት በመባል ይታወቃል።ለምሳሌ ውሃ፣ መንገድ፣ ትምህርት ቤት እና ሆስፒታል የጋራ ንብረቶች ናቸው። ስለዚህ ሰዎች እነዚህን በጋራ የሚጠቀሙባቸውን ነገሮች መጠበቅ እና መንከባከብ አስፈላጊ ነው።

### ተግባር 1.

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።**

1. ከዚህ በላይ ባለው ምስል ላይ ምን ምን ነገሮች ይገኛሉ?
2. በምስሉ ላይ ያሉሰዎች ምን እየሰሩ ይገኛሉ?

# ትምህርት 2. ውሃ

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃቶች

- ውሃ የጋራ ሀብት መሆኑን ትናገራለህ/ሽ።
- የውሃን ንጽህና መጠበቅ የማን ድርሻ እንደሆነ ትገልጻለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄ

1. ውሃ የጋራ ሀብት ነው? ለምን?
2. የውሃን ንጽህና መጠበቅ የማን ድርሻ ነው?



ማህበረሰብ ውሃን በጋራ ሲጠቀም



ውሃን ለግል ንጽህና መጠበቂያና ለእጽዋት መጠቀም

ውሃ አንድ ማህበረሰብ ከሚጠቀምባቸው የጋራ ሀብቶች ውስጥ አንዱ ነው። ንጹህ ውሃ ለመጠጥ እና ምግብ ለማብሰል ያገለግላል። የግል ንጽህናችንን ለመጠበቅም ያግዘናል። እጽዋትን ውሃ በማጠጣት እንንከባከባቸዋለን። ስለዚህ የውሃን ንጽህና መጠበቅ እና ሳያባክኑ መጠቀም የሁሉም ማህበረሰብ ሃላፊነት ነው።

## ተግባር 2.

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጭ።

1. ውሃ የግል ሀብት ነው።

   ሀ. እውነት ለ. ውሸት

2. የጋራ ንብረትን እንደ የግል ንብረታችን መንከባከብ ይገባናል።

   ሀ. እውነት ለ. ውሸት

3. በውሃ የሚጠቀመው የሰው ልጅ ብቻ ነው።

   ሀ. እውነት ለ. ውሸት

4. ከሚከተሉት የውሃ ጥቅም የሚያመለክተው የቱ ነው?

   ሀ. ለመጠጥ እና ምግብ ለማዘጋጀት

   ለ. የግል ንጽህናን ለመጠበቅ

   ሐ. እጽዋትን ለመንከባከብ

   መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

# ትምህርት 3. ትምህርት ቤት

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃት

- ትምህርት ቤት የጋራ ንብረት መሆኑን ትገልጻለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄ

ትምህርት ቤት የግል ንብረት ነው? ወይስ የጋራ ንብረት ነው?



ትምህርት ቤት ተማሪዎች እውቀት የሚገበዩበት ቦታ ነው። ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙትን ንብረቶች በጋራ ይጠቀሙበታል። ለምሳሌ፣ ወንበር ፤ የጥቁር ሰሌዳ፣ መጸዳጃ ቤት እና የመሳሰሉት ተማሪዎች በጋራ የሚጠቀሙባቸው የጋራ ንብረቶች ናቸው። ስለዚህ እነዚህን ንብረቶች በአግባቡ መጠቀም እና መንከባከብ አስፈላጊ ነው።

# ለትምህርት ቤት የተዘመረ መዝሙር

## ትምህርት ቤቲ

ትምህርት ቤቲዋ የምማርብሽ

ሁሉን አሳልፊ የማስታውስሽ

መማር ያኮራኛል ዐይኒን ከፍቶልኛል

እኒስ በበኩሊ ትምርት ይሻለኛል

## ተግባር 3.

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ።

1. ትምህርት ቤት የጋራ ንብረት ነው፡፡

   ሀ. እውነት　　　ለ. ውሸት

2. ወንበር ላይ ወጥቶ በእግር መቆም ትክክል አይደለም።

   ሀ. እውነት　　　ለ. ውሸት

3. ልጆች በመጸዳጃ ቤት በትክክል መጠቀም ያለባቸው ለምንድን ነው?

   ሀ. ለጤንነታቸው　　　ሐ. የወል ንብረት ስለሆኑ ነው

   ለ. ለንጽህናቸው　　　መ. ሁሉም መልስ ናቸው

4. ትምህርት ቤትን የሚገልጽ የቱ ነው?

   ሀ. የእውቀት ምንጭ ነው፡፡　　　ሐ. የመደሰቻ ቦታ ነው፡፡

   ለ. የምሁራን መፍለቂያ ነው፡፡　　　መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

# ትምህርት 4. መንገድ

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃት

- መንገድ የጋራ ንብረት መሆኑን ትገልጻለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄ

**መንገድ የጋራ ንብረት ነው? ለምን?**



በመንገድ ሁሉም ሰው ይጠቀምበታል። በእግር፣ በፈረስ፣ በመኪና እና በባቡር የሚጓዙ ሰዎች በመንገድ ይገለገላሉ። ልጆችም በመንገድ በመጠቀም ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ፡፡ ከትምህርት ቤት ወደ ቤትም ይገባሉ። ለዚህ ነው መንገድ የጋራ ንብረት ነው የምንለው። ስለዚህ በመንገድ ስንጠቀም ጥንቃቄ ማድረግ እና የመንገድ የጥንቃቄ ሕጎችን መጠበቅ አለብን።

## ተግባር 4.

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ።

1. መንገድ በንጽህና መያዝ አለበት።

   ሀ. እውነት    ለ. ውሸት

2. ሰዎች በምን በምን ከቦታ ቦታ ይጓጓዛሉ?

   ሀ. በባቡር    ሐ. በበቅሎ

   ለ. በእግር    መ. ሁሉም መልስ ይሆናል

3. የመንገድ ጥንቃቄ ሕጎች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

   ሀ. ግራ እና ቀኝ በማየት መንገድ ማቋረጥ

   ለ. ለብቻ ሆኖ መንገድ አለማቋረጥ

   ሐ. የትራፊክ ሕግን ማክበር

   መ. ሁሉም

## ማጠቃለያ

የጋራ ንብረት ሰዎች ሁሉ የሚጋሩት እና በጋራ የሚጠቀሙበት ነው። ከጋራ ንብረቶች መካከል ጥቂቶቹ መንገድ፣ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል ናቸው። እንዲሁም ውሃ ሰዎች በጋራ የሚጠቀሙበት የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡ እነዚህን ንብረቶች ሁሉም ሰው በዕድሜ፣ በጾታ፣ በሀይማኖት፣ በባህል እና በዘር ሳይገደቡ በጋራ ይጠቀሙበታል። ስለዚህ ሁሉም ሰው የጋራ ንብረቶችን መጠበቅ እና መንከባከብ አለበት።

# የክለሳ ጥያቄዎች

## I. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ውሸት " በማለት መልስ/ሺ።

1. ሌብነት የጋራ ንብረትን የሚጎዳ መጥፎ ተግባር ነው።
2. የጋራ ንብረቶችን የሚጠብቁት ፖሊሶች ብቻ ናቸው።
3. ደብተራችንን የምናስቀምጥበት ቦርሳ የጋራ ንብረት ነው።
4. የጋራ ንብረት ለሁሉም ሰው አስፈላጊ ነው።
5. በጋራ ንብረት በትክክል መጠቀም አለብን።

## II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጥ/ጪ።

1. ከሚከተሉት የግል ንብረት ያልሆነው የትኛው ነው?

    ሀ. ብዕር

    ለ. ትምህርት ቤት

    ሐ. ደብተር

    መ. ጫማ

2. የጋራ ንብረትን የመንከባከብ ተግባር የሆነው የቱ ነው?

    ሀ. ዕፅዋትን መትከል እና መንከባከብ

    ለ. ንብረትን በአግባቡ መጠቀም

    ሐ. የአከባቢያችንን ንጽህና መጠበቅ

    መ. ሁሉም መልስ ናቸው

3. የጋራ ንብረት የሆነው የቱ ነው?

    ሀ. ሆስፒታል

    ለ. መንገድ

    ሐ. ጥቁር ሴሌዳ

    መ. ሁሉም መልስ ናቸው

4. በጋራ ንብረት የሚጠቀመው ማን ነው?

    ሀ. ተማሪዎች ብቻ

    ለ. ባለሀብቶች ብቻ

    ሐ. መምህራን ብቻ

    መ. ሁሉም ማህበረሰብ

5. የጋራ ንብረትን መንከባከብ ያለበት ማን ነው?

    ሀ. መምህራን ብቻ

    ለ. ድሆች ብቻ

    ሐ. ተማሪዎች ብቻ

    መ. ሁሉም ማህበረሰብ

# ምዕራፍ 6

# ባህላዊ ቅርሶች

## የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

- ባህላዊ ቅርሶች ምን እንደሆኑ መናገር፤
- የተለያዩ ባህላዊ ቅርሶችን መለየት፤
- ባህላዊ ቅርሶችን መንከባከብ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት፤
- ለባህላዊ ቅርሶቸ የሚደረጉትን እንክብካቤዎች መለየት ናቸው።

## ትምህርት 1. የባህላዊ ቅርሶች ምንነት

### ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃት

- ባህላዊ ቅርሶችን ትለያለህ/ሽ፡፡

### የግንዛቤ ጥያቄ

ባህል ማለት ምን ማለት ነው?

ባህል የአንድ ማህበረሰብ ማንነት የሚገለጽበት ነው። ባህል በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡ ልብስ፣ ምግብ፣

ግብረገብ፣ እሴት፣ ልማድ፣ እና የመሳሰሉት ናቸው።




## ተግባር 1.

1. ከላይ የቀረቡት ምስሎች ምን ምን ያመለክታሉ?
2. ባህላዊ ቅርሶች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

ባህላዊ ቅርሶች የቀድሞ ትውልድን ዕውቀት፣ሀይማኖት፣ባህል፣ እሴት እና ዕውቀት የሚያሳዩ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የቆዩ ናቸው። ከእነዚህም መካካል ጥንታዊ ሕንጻዎች፣ የበአላት አከባበር፣ ሀውልቶች፣ በአደባባይ የሚከበሩ በዓላት፣ ባህላዊ ልብሶች እና ባህላዊ ምግቦችን ጥቂቶቹ ናቸው።

## ለምሳሌ፡



የአባ ጅፋር ቤተመንግስት



የእሬቻ በዓል አከባበር



ድሬ ሼከና ሁሴን

## ተግባር 2.

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጭ።

1. ባህል የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ ምልክት ነው።

   ሀ. እውነት ለ.ውሸት

2. ባህላዊ ቅርሶች የድሮ ሰዎችን ታሪክ ይገልጻሉ።

   ሀ. እውነት ለ. ውሸት

3. የአንድ ማህበረሰብ ባህል በምን ሊገለጽ ይችላል?

   ሀ. ልብስ ሐ. ግብረገብ እና እሴት

   ለ. ምግብ መ. ሁሉም

4. ባህላዊ ቅርስ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. የአባ ጅፋር ቤተ መንግስት

   ለ. ድሬ ሼክና ሁሴን

   ሐ. የእሬቻ በዓል

   መ. ሁሉም መልስ ነው

5. የበዓል ቀን በምን ይታወሳል?

   ሀ. በባህላዊ ልብስ ሐ. በባህላዊ ምግብ

   ለ. በባህላዊ ጨዋታ መ. ሁሉም መልስ ነው

# ትምህርት 2. የባህላዊ ቅርስ ዓይነቶች

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ውጤት

- ባህላዊ ቅርሶችን ትዘረዝራለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄ

በአከባቢህ/ሽ ያሉ ባህላዊ ቅርሶች ዘርዝር/ሪ?

ባህላዊ ቅርሶች በሁለት ይከፈላሉ። እነሱም፡- የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች ።

## ሀ. የሚዳሰሱ ቅርሶች

የሚዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች በዓይን የሚታዩና በእጅ የሚዳሰሱ ናቸው። ለምሳሌ፡ ቤተመንግስት፣ አዳራሾች፣ ሀውልቶች እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡





የአባ ጅፋር ቤተመንግስት

የኩምሳ ሞሮዳ ቤተመንግስት



የጨለንቆ ሀውልት



የሶፍዑመር ዋሻ

## ለ. የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች

እነዚህ በዓይን የማይታዩና በእጅ የማይዳሰሱ ቅርሶች ናቸው። ለምሳሌ ቋንቋ፣ ስነቃል፣ ግብረገብ፣እሴት፣ ዘፈኖች እና የመሳሰሉት ናቸው።

## ተግባር 3.

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጭ።**

1. የሚዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች የሆኑት የትኞቹ ናቸው?
   - ሀ. የአባ ጅፋር ቤተ መንግስት
   - ለ. የአኖሌ ሀውልት
   - ሐ. ድሬ ሼከና ሁሴን
   - መ. ሁሉም መልስ
2. የሚዳሰሱ ባህላዊ ቅርስ ያልሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ግብረገብ እና እሴቶቸ
   - ለ. ቋንቋ
   - ሐ. የጨለንቆ ሀውልት
   - መ. ስነቃል
3. በዓይን የሚታዩ ባህላዊ ቅርሶች____________ይባላሉ።
4. የኩምሳ ሞሮዳ ቤተመንግስት የሚዳሰስ ባህላዊ ቅርስ ነው።
   - ሀ. እውነት
   - ለ. ውሸት
5. በዓይን የማይታዩ ባህላዊ ቅርሶች____________ይባላሉ።

# ትምህርት 3. የባህላዊ ቅርስ ጥቅም

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ውጤት

- የባህላዊ ቅርሶችን ጥቅም ትናገራለህ/ሽ።

## የግንዛቤ ጥያቄ

ባህላዊ ቅርሶች ምን ምን ጥቅሞች አሏቸው?

ባህላዊ ቅርሶች የሰውን ልጅ ታሪክ እና ስልጣኔ ለመረዳት ያገለግላሉ።



ባህላዊ ቅርሶች የተለያዩ ጥቅሞች አሏቸው። ለምሳሌ፡







ሀ. ለጉብኝት እና ለትምህርት ይውላሉ



ለ. ገቢ ያስገኛሉ



# ትምህርት 4. ባህላዊ ቅርሶችን መንከባከብ

## ቢያንስ ልትጎናጸፍ/ፊ የሚገባ የመማር ብቃት

- ባህላዊ ቅርሶች የሚንከባከቡበትን መንገድ ይለያሉ።

## የግንዛቤ ጥያቄ

ባህላዊ ቅርሶችን የሚጎዱ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ባህላዊ ቅርሶች የቀደምት ቅርጻቸውን፣ ቀለም፣ ጠባይ እና የመጀመሪያ ትርጉማቸውን እንዳይለቁ እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል። ባህላዊ ቅርሶችን ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ በተለያዩ መንገዶች መንከባከብ እንችላለን። ለምሳሌ፡

- ከስርቆት እና ከተለያዩ ጉዳቶች መጠበቅ
- እንዳይሰባበሩ ጥበቃ ማድረግ
- የተሰባበሩትን መጠገን



ትክል ድንጋይ



የባቢሌ ትክል ድንጋይ



የጅማ አባጅፋር
ቤተመንግስት



የኩምሳ ሞሮዳ
ቤተመንግስት

# ማጠቃለያ

ባህላዊ ቅርሶች የሚባሉት ያለፉት ትውልድ ታሪክ ሆኖ እንደ ዕውቀት፣ ሀይማኖት፣ ባህል፣ እሴት፣ የኑሮ ሁኔታ፣ ግብረገብ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። ይህም የሚያገለግለው ያለፈን ትውልድ ታሪክ አሁን ካለው ትውልድ ጋር በማገናኘት ለሚመጣ ትውልድ ለማስቀመጥ ነው። ስለዚህ ባህላዊ ቅርሶች የያለፈው ትውልድ እምቅ ልምድ ማሳያ ናቸው።

ባህላዊ ቅርሶች ምጣኔያዊ ሀብት፣ ማህበረሰባዊ እና ፖለቲካዊ ጥቅም አላቸው። እነዚህም ቅርሶች የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች በመባል በሁለት ይከፈላሉ። ባህላዊ ቅርሶች በተፈጥሮ እና በሰው ሰራሽ አደጋዎች ሊጎዱ ስለሚችሉ መጠበቅ እና መንከባከብ አለብን።

# የክለሳ ጥያቄዎች

## I. በ“ሀ” ረድፍ የተዘረዘሩትን በ “ለ” ስር ከቀረቡት ጋር አዛምድ/ጂ።

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. የኦሮሞ ህዝብ የኑሮ ሁኔታ ገላጭ | ሀ. የአኖሌ ሀውልት |
| 2. የቅርሶች ጉብኝት | ለ. በዓል |
| 3. የሚዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች | ሐ. ቱሪዝም |
| 4. የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች ቅድሚያ መስጠት | መ. ለአዛውንቶች |
| 5. አዛውንቶችን ማክበር | ሠ. የኦሮሞ ሕዝብ እሴቶች |

## II. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ “እውነት” ትክክል ካልሆኑ ደግሞ “ውሸት ” በማለት መልስ/ሺ።

1.ባህላዊ ቅርሶች ይጎበኛሉ።

2.ሁሉም ዜጋ ባህላዊ ቅርሶችን መጠበቅ እና መንከባከብ አለባቸው።

3. ባህላዊ ቅርሶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱት የሰው ልጆች ብቻ ናቸው።

4. የአኖሌ ሀውልት ከሚዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች አንዱ ነው።